## 30th ANNUAL ORDINARY AND 12th EXTRAORDINARY GENERAL MEETINGS OF SHAREHOLDERS

Notice is hereby given to the Shareholders to attend the 30th Annual Ordinary and 12th Extraordinary General Meetings of Awash Insurance S.C. which will be held in accordance with Article 393(1) and Article 400(1) of Commercial Code of Ethiopia, Proclamation Number 1243/2021 as well as Article 8(a) of the Memorandum of Association of the Company. Awash Insurance S.C. has a subscribed capital of Birr 3,850,185,500 and paid-up capital of Birr 1,921,492,300 as at June 30, 2024; Business Registration Certificate Number of the Company is አአ/ገማ-3-1532/87 from the Trade Bureau, Insurance Business License Number 003/94 issued by the National Bank of Ethiopia, and the Company's Headquarters is at Awash Towers, Addis Ababa, Kirkos Subcity, Woreda 7. The General meetings will be held on Saturday, October 26, 2024 at Addis Ababa Hilton Hotel starting from 8:00 a.m. to transact the following business:

**AGENDA FOR 30th ANNUAL ORDINARY GENERAL MEETING**

1. Notification of Share Transfers, Share Sales and New Shareholders who acquired shares in 2023/24;
2. Consideration and approval of the 2023/24 Annual Report of Board of Directors;
3. Consideration and approval of the 2023/24 Annual Report of Auditors;
4. Deliberation on and approval of the proposed appropriation of 2023/24 profits;
5. Approval of Annual Compensation of Board of Directors for 2023/24;
6. Approval of Board of Directors' monthly allowance for 2024/25;
7. Approval of the Auditors' Annual Fee for 2024/25; and
8. Election of the members of Board Nomination and Election Committee.

**AGENDA FOR 12th EXTRAORDINARY GENERAL MEETING**

- Amendment of the Memorandum of Association of Awash Insurance S.C.

**N.B.**

Shareholders who are not able to attend the meetings in person may sign and return the proxy form and give one copy to the designated agent and the second copy along with the copy of renewed identification card of a shareholder to be submitted to the Company's CEO office, on the 2nd floor of Awash Towers, three days before the meeting date.

By Order of the Board of Directors

## የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔና 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

የአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በኢትዮጵያ ንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 393(1) እና አንቀጽ 400(1) እንዲሁም በኩባንያው መመስረቻ ፅሁፍ አንቀጽ 8(ሀ) መሠረት በሚደረገው 30ኛ ዓመታዊ መደበኛና 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ እንዲገኙ መስታወቂያ ተሰጥቷል።

ኩባንያው የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቁጥር አአ/ገግ-3-1532/87 ከንግድ ቢሮ እንዲሁም የመድን ሥራ ፍቃድ ቁጥር 003/94 ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠው ሲሆን እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2024 ላይ የኩባንያው የተፈረመ ካፒታል ብር 3,850,185,500፣ የተከፈለ ካፒታል ብር 1,921,492,300 ደርሷል።

የኩባንያው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አዋሽ ታወርስ ላይ ይገኛል።

ጠቅላላ ጉባዔዎቹ ቅዳሜ ጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ከጠዋቱ 2 ሰዓት ጀምሮ የሚካሄዱ ሲሆን የሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ይወያያል፣

### የ30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ

1. እ.ኤ.አ. በ2023/24 የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮች፣ የአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭና አዲስ ባለአክሲዮኖችን ማሳወቅ፣
2. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣
3. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣
4. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የትርፍ ክፍፍል ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ማፅደቅ፣
5. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣
6. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የዲሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል መወሰን፣
7. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የኦዲተሮችን ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣
8. የዲሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ማካሄድ።

### የ12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ

-የአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል።

**ማሳሳቢያ**

በጉባዔዎቹ ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች የውክልና ፎርሙን ፈርመው በመመለስ አንድ ኮፒ ለተመደበው ወኪል እንዲሁም 2ኛውን ኮፒ ከታደሰው የባለአክሲዮኑ መታወቂያ ካርድ ጋር በማያያዝ ለጉባዔዎቹ 3 ቀናት ሲቀረው አዋሽ ታወርስ 2ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ማስገባት ይችላሉ።

**በዲሬክተሮች ቦርድ ትዕዛዝ**

# የአዋሽ ኢንሹራንስ አክስዮን ማኅበር
# የተሻሻለ መመሥረቻ ፅfከፍ

**<u>መግቢያ</u>**

አዋሽ ኢንሹራንስ አክስዮን ማኅበር የመመሥረቻ ጽfከፍ እና መተዳደሪያ ደንቡ መስከረም 05 ቀን 1987 ዓ.ም በወቅቱ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተረጋግጦ እና ተመዝግቦ የመድን ሥራን ስለመፍቀድ እና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 መሠረት ተቋቁሞ በመሥራት ላይ ያለ የመድን ተቋም ሲሆን፣

የንግድ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 በመሻሻሉ እና የንግድ ሕጉም የአክስዮን ማኅበራትን መተዳደሪያ ደንብ ዕውቅና የማይሰጥ በመሆኑ፣ የንግድ ሕግ አንቀጽ 255 የአክስዮን ማኅበር ለማቋቋም እና ለመምራት አስፈላጊው ሰነድ የመመሥረቻ ጽfከፍ ብቻ መሆኑን በመደንገጉ፣

ስለሆነም፣ ከላይ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ እና ከብሔራዊ ባንክ የመድን ኮርፖሬት አስተዳደር መመሪያ ጋር በማጣጣም፣ በተለያየ ጊዜ በኢንሹራንስ ኩባንያው ጠቅላላ ጉባዔ ከተያዙ ቃለ ጉባዔዎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች በማካተት እና በሥራ ላይ ያሉትን የአክስዮን ማኅበሩን የመመሥረቻ ጽfከፍ ከመተዳደሪያ ደንቡ ጋር በአግባቡ በማዋሃድ የተዘጋጀውን ይህንን የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽfከፍ የአክስዮን ማኅበሩ ባለአክስዮኖች 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ አፀድቋል፡፡

## <u>አንቀጽ አንድ</u>
## <u>የአክስዮን ማኅበሩ መጠሪያ</u>

የማኅበሩ መጠሪያ ‘’አዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር” ነው፡፡ ከዚህ በኋላ "አክስዮን ማኅበር" በሚል ይጠቀሳል፡፡

## <u>አንቀጽ ሁለት</u>
## <u>የአክስዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፎች</u>

2.1. የአክስዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡

2.2. ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እና አግባብነት ባላቸው ህጎች እና መመሪያዎች መሰረት ከኢትዮጵያ ውጭ ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ሦስት

## የአክስዮን ማኅበሩ ዓላማዎች

የአክስዮን ማኅበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

3.1. በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የጠቅላላ መድን ሥራ እና የረጅም ጊዜ መድን ሥራን ማከናወን፣
3.2. ከጠቅላላ መድን ሥራ እና ከረጅም ጊዜ መድን ሥራን ጋር ቁርኝት ያላቸውን ተቀፅላ ስራዎችን መስራት፣
3.3. አግባብነት ባላቸው ህጎች እና መመሪያዎች መሰረት በሌሎች ኢንሹራንስና የሪኢንሹራንስ /ጠለፋ ኢንሹራንስ/ ድርጅቶች ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ፣
3.4. የሪል እስቴት ስራዎችን መስራት እና በተለያዩ የመድን ተቋማት እንዲሳተፉባቸው የሚፈቀዱ የንግድ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣
3.5. በካፒታል ገበያ ሥራ ላይ መሣተፍ፣
3.6. የታካፉል አገልግሎት መስጠት፣
3.7. በኢንቨስትመንት የማማከርና ሀብት የማስተዳደር አገልግሎቶችን መስጠት፤
3.8. የመድን ተቋማት እንዲሳተፉባቸው የሚፈቀዱ መረጃ የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤
3.1. ባለአደራ ሆኖ የመሥራት ተግባር ማከናወንና የተፈቀዱ የንግድ ዋስትናዎችን መስጠት፤
3.2. በዲጂታል ዘዴዎች የመድን እና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚመለከተው በተቆጣጣሪ የመንግስት አካል የሚፈቀዱለትን አገልግሎቶች መስጠት፣

## አንቀጽ አራት

## የአክስዮን ማኅበሩ ካፒታል /ዋና ገንዘብ/

4.1. የአክስዮን ማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር ......................... /... ..........ቢሊዮን/ ነው፡፡
4.2. አክስዮን ማኅበሩ የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ አምስት መቶ ብር /500/ በሆነ .........................ሚሊዮን /........................./ አክሲዮኖች የተከፋፈለ፣ የተከፈለ ካፒታል ብር ............................ሚሊዮን /.....................   / ካፒታል አለው፡፡

## አንቀጽ አምስት

## የባለአክሲዮኖች ትርፍ ክፍፍል

በእያንዳንዱ የሂሣብ መጨረሻ በአክስዮን ማኅበሩ ኦዲተሮች ከተረጋገጠው ትርፍ በሕግ፣ በመመሥረቻ ጽfከፍ እና በጠቅላላው ጉባኤ ውሣኔ መሠረት የሚቀነሱ ሂሣቦች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪው የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው ክፍያ የተፈፀመባቸው አክሲዮኖች በአመቱ ውስጥ የነበራቸውን ቆይታ ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት

ባለአክሲዮኖቹ ለአክስዮን ማኅበሩ ግዴታዎች ኃላፊ የሚሆኑት በተፈረመው የአክሲዮን ድርሻ መጠን ብቻ ነው።

## አንቀጽ ሰባት

## የአክሲዮኖች ዓይነት

7.1. የአክስዮን ማኅበሩ አክሲዮኖች በባለአክስዮኖች ስም የሚመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ።

7.2. የአክስዮን ማኅበሩ አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ናቸው።

7.3. ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የአክስዮን ማኅበሩ አክሲዮን የጋራ ባለሀብት ከሆኑ የንግድ ሕግ አንቀፅ 270 ተፈጻሚ ይሆናል።

7.4. አክሲዮኖች የሚወጡት በሙሉ እንደተከፈለባቸው ይሆናል ።

7.5. አክሲዮኖችን ከተጻፈባቸው በላይ በሆነ ዋጋ ለማውጣት ይቻላል።

## አንቀጽ ስምንት

## የአክሲዮን ምስክር ወረቀት እና ባለአክሲዮኖች መዝገብ

8.1. እያንዳንዱ በወረቀት የሚሰጥ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በንግድ ሕጉ የተደነገገውን ዝርዝር መያዝ አለበት።

8.2. የአክስዮን ማኅበሩ የባለአክስዮኖች መዝገብ በንግድ ሕጉ የተደነገገውን ዝርዝር የሚያያካትት ሆኖ በዋና መሥሪያ ቤት መያዝ አለበት። መዝገቡ በወረቀት ወይንም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀመጥ ይችላል።

8.3. መዝገቡ ለባለአክስዮኖች ነፃ ምርመራ ክፍት ይሆናል።

8.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ግልባጮችንና ተነጣይ ግልባጮችን ለመውሰድ የሚከፈለውን ዋጋ ይወስናል።

## አንቀጽ ዘጠኝ

## መያዣነትና የአላባ ጥቅም

የአክስዮን ማኅበሩ አክሲዮኖች በመያዣነት ወይም በአላባ ጥቅም ከተሰጡ የንግድ ሕጉ አንቀፅ 271 ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ አስር

## አክሲዮኖችን ስለማስተላለፍ

10.1. የአክስዮን ማኅበሩን አክስዮኖች ለማስተላለፍ ይቻላል።

10.2. አዲስ አክስዮኖች ሲወጡ ባለአክስዮኖች በቀደምትነት የመግዛት መብት አላቸው።

10.3. አፈፃፀሙ በንግድ ህጉ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ዝርዝር መመሪያ መሰረት ይሆናል።

10.4. አክሲዮኖችን የማስተላለፍ ተግባር በባለአክሲዮኖች መዝገብ ካልተመዘገበ አክስዮን ማኅበሩን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።

## **<u>አንቀጽ አስራ አንድ</u>**

## **<u>የአክስዮን ማኅበሩ አካላት</u>**

አክስዮን ማኅበሩ የሚከተሉት ዋና ዋና አካላት ይኖሩታል፡-

11.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣
11.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
11.3. ኦዲተሮች፣
11.4. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ እና
11.5. የአክስዮን ማኅበሩ ፀሀፊ።

## **<u>አንቀጽ አስራ ሁለት</u>**

## **<u>የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ</u>**

12.1. ማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የአክስዮን ማኅበሩ ከፍተኛ የአመራር አካል ሲሆን ውሣኔዎቹ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራዋል።

12.2. የጠቅላላ ጉባኤዎች ባለአክሲዮኖቹን በሙሉ የሚጠቀልሉ ሆነው መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆኑ ይችላሉ።

12.3. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣ በብሔራዊ ባንክ፣ በፍ/ቤት ትዕዛዝ፣ በሂሳብ አጣሪዎች ሊደረግ ይችላል::

12.4. ባለአክስዮኖች በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክስዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በጽfhፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይቻላል ::

12.5. በጉባዔው ላይ የተገኙትን ተሳታፊዎች ወይም ወኪሎቻቸውን ስምና አድራሻ፣ እያንዳንዳቸው ያላቸውን የአክስዮን ብዛትና የሚሰጠውን የድምፅ ቁጥር የሚያሳይና በተሳታፊዎች የሚፈረም የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ ይቀመጣል፤ ሰነዱም በአክስዮን ማኅበሩ ፀሐፊ ፊርማ ይረጋገጣል::

12.6. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380 መሠረት ፈቃደኛ ከሆኑ በባለአክስዮንነትም ሆነ በወኪልነት ስም በጉባዔው ላይ ከተገኙት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው አባላት መካከል በሚደረግ ስምምነት የተወሰኑት ባለአክስዮኖች ድምጽ ቆጣሪዎች ይሆናሉ፤ ከፍተኛ ድምፅ ያላቸው እነዚህ ባለአክስዮኖች ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ሌላ ሰው መምረጥ ካልፈለጉ ጉባዔው ድምፅ ቆጣሪዎችን መምረጥ ይኖርበታል::

## አንቀጽ አስራ ሶስት

## የጉባዔው አጠራር

13.1. ለጉባዔው የሚደረግ ጥሪ በመገናኛ ብዙሃን በሚወጣ ማስታወቂያ ወይም ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሚላክኢሜይል ወይንም ሞባይል መልእክት ወይንም አመቺ በሆነ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ሊሆን ይችላል።

13.2. የጥሪው ዝርዝር ይዘት በንግድ ሕጉ እንደተመለከተው ይሆናል።

## አንቀጽ አሥራ አራት

## የጉባኤው አጀንዳ

የጉባዔው አጀንዳ በጠቅላላ ጉባኤውን በጠራው አካል ይዘጋጃል።

## አንቀጽ አሥራ አምስት

## የባለአክሲዮን እንደራሴ

15.1. ማንኛውም ባለአክሲዮን በአክስዮን ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚወክለውን አንድ እንደራሴ ለመሾም ይችላል።

15.2. ባለአክሲዮኑ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማኅበር ከሆነ እንደራሴው በወካዩ ድርጅት ይሰየማል። የእንደራሴ አሰያየም ስርአትን የተመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናሉ።

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የጠቅላላ ጉባዔው አመራር

16.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም፣ እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም ምክትል ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ፣ ከዳይሬክተሮቹ በሥራ ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል ቀደምትነት ያለው በማይኖርበት ጊዜ ጉባዔው የሚመርጠው ሰው ሰብሳቢ ይሆናል።

16.2. የአክስዮን ማኅበሩ ፀሐፊ የጉባዔው ፀሐፊ ይሆናል፡፡ የጉባዔው ፀሐፊ በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢው ከአባሎች መካከል ወይም ከውጭ አንድ የጉባዔ ፀሐፊ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስመድባል፡፡

16.3. የጉባኤው ውይይቶችና ውሳኔዎች በፅሁፍ ተደርገውና በስብሰባው ላይ በተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና በአክስዮን ማኅበሩ ፀሀፊ ተፈርመው በንግድ ህጉ መሰረት በቃለ ጉባዔ መዝገብ ይገለበጣል፤ ቃለ ጉባዔው ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በአክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት።

## **አንቀጽ አሥራ ሰባት**
## **ድምጽ የመስጠት መብት**

17.1. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረዋል።

17.2. የአንድ ባለአክሲዮን ወይም የአንድ እንደራሴ ጥቅም ከአክስዮን ማኅበሩ ጥቅም ጋር የሚጋጭበት ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩ የሚመለከተው ባለአክሲዮን ወይም እንደራሴ ድምፅ አይሰጥም።

17.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የእነርሱን ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የተመለከቱ እና የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮችን በሚመለከት ድምፅ አይሰጡም።

## **አንቀጽ አሥራ ስምንት**
## **የጠቅላላ ጉባኤዎች ጊዜ**

18.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ከአክስዮን ማኅበሩ የሂሣብ ዓመት መጨረሻ ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ባለው የስድስትወራት ጊዜ ውስጥ እና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤

18.2. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ እና ሊሰበሰብ ይችላል።

## **አንቀጽ አስራ ዘጠኝ**
## **የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልአተ ጉባኤና የድምፅ ብልጫ**

19.1. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልአተ ጉባኤ የሚኖረው፣

**ሀ.** በመጀመሪያ ጥሪ ሲሆን፣ ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ የሩብ (1/4ኛ) ሲገኙ፣

**ለ.** በሁለተኛ ጥሪ ሲሆን፣ በስብሰባው ላይ ቁጥራቸው ማናቸውንም ያህል የሆነ አክሲዮኖች ሲገኙ ይሆናል።

19.2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚያልፉት ተራ በሆነ የድምጽ ብልጫ ነው፣ ድምፅ ያልሰጡትም ሆነ ያልተጻፈባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም። በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም የጉባዔው ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ለውሳኔ የሚሰጠውን ድምፅ መቁጠር ይቻላል።

## **አንቀጽ ሀያ**
## **የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልአተ ጉባኤና ድምፅ ብልጫ**

20.1. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልአተ ጉባኤ የሚኖረው፣

**ሀ.** በመጀመሪያ ጥሪ ሲሆን ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ ከሶስት የአንድ እጅ (1/ 3ኛ) አክስዮኖች፣

**ለ.** በሁለተኛ ጥሪ ሲሆን ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ ከአራት የአንድ እጅ (1/4ኛ) አክስዮኖች፣

**ሐ.** በሶስተኛ ጥሪ ሲሆን ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው በስብሰባው ላይ ቁጥራቸው ማናቸውንም ያህል የሆነ አክሲዮኖች ሲገኙ ይሆናል፡፡

20.2. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚያልፉት ከተሰጠው ድምፅ ከሶስቱ እጅ በሁለት (2/3ኛ) ሲደገፉ ይሆናል፣ ድምፅ ያልሰጡትም ሆነ ያልተጻፈባቸው የድምፅ ውሳኔ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም የጉባዔው ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ለውሳኔ የሚሰጠውን ድምፅ መቁጠር ይቻላል፡፡

20.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ የተደነገገው ቢኖርም፣

**ሀ.** የአክስዮን ማኅበሩን ዜግነት ለመለወጥ፣

**ለ.** በአክሲዮኖች ላይ የተፃፈውን ዋጋ (ፓር ቫልዩ) በመጨመር የአክስዮን ማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ፣ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው በሙሉ መገኘትና ውሳኔውን በአንድ ድምጽ መደገፍ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሀያ አንድ

## የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

21.1. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣**ሀ.** የመመሥረቻ ጽሁፍን ለማሻሻል፤

**ለ.** የአክስዮን ማኅበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይንም የመቀነስ፤**ሐ.** የአክስዮን ማኅበሩን ዜግነት መለወጥ፤

**መ.** አክስዮን ማኅበሩ እንዲፈርስ፤ ወይም ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማኅበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፤ እንዲሁም፤

**ሠ.** አግባብነት ባላቸው ሕጎች በዚህ ጉባዔ እንዲታዩ ተለይተው የተሰጡትን ጉዳዮች የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፣

21.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

**ሀ.** አግባብ ባለው ህግ መሰረት የአክስዮን ማኅበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመርጣል፣ ይሽራል፣ የስራቸውን ዋጋ እና አበል ይወስናል፣

**ለ.** የአክስዮን ማኅበሩን ኦዲተሮች ይሾማል፣ ይሽራል፣ የሥራቸውንም ዋጋ ይወስናል፣

**ሐ.** የዳይሬክተሮችንና የኦዲተሮችን ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣የአክስዮን ማኅበሩን የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መርምሮ ያፀድቃል፤

**መ.** በትርፍ አከፋፈልና ካለፈው የአክስዮን ማኅበሩ ሂሣብ ጋር በተያያዘ ማናቸውም ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

**ሠ.** ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ተለይተው ያልተሰጡ ሌሎች ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ ሀያ ሁለት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ

22.1. የአክስዮን ማኅበሩን ሥራ የሚመሩት ጠቅላላ ጉባዔው መርጦ የሚሾማቸው 9 /ዘጠኝ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይኖሩታል፡፡

22.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነት አክስዮን ማኅበሩን ይወክላሉ፡፡

22.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሥራ ዘመን 3 /ሶስት/ ዓመት ይሆናል፡፡

22.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ለተከታታይ ሁለት የስራ ዘመን ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ለሥራው ቀጣይነት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሦስተኛ የሥራ ዘመን በድጋሚ የሚመረጡበት እና በጎደሉት የሚተኩበት አኳኋን አግባብነት ባለው መመሪያ መሠረት የሚወሠን ይሆናል፡፡

22.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ከወረቀት በሚዘጋጅ የምርጫ ካርድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊካሄድ ይችላል፤

ለዳይሬክተሮቹ የተሰጠው ድምፅ ቆጠራም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊካሄድ ይችላል፡፡

22.6. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከመካከላቸው አንድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ይመረጣሉ፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

22.7. የአክስዮን ማኅበሩ ፀሀፊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፀሀፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሀያ ሶስት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

23.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

**ሀ.** የጠቅላላ ጉባዔ የሚያስተላልፋቸውን መመሪያዎች እና ውሳኔዎችን ተከታትሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**ለ.** የአክስዮን ማኅበሩ ስራዎች በህግ መሰረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ የሥራ እንቅስቃሴውን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

**ሐ.** የአክስዮን ማኅበሩን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ያፀድቃል፣

**መ.** የአክስዮን ማኅበሩን እስትራቴጂክ እቅድ፤ ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፣

**ሠ.** የአክስዮን ማኅበሩን ድርጅታዊ መዋቅር እና የደመወዝ መደብ /ስኬል/ ያፀድቃል፣

**ረ.** አክስዮን ማኅበሩ ጤናማ የፋይናንስ አስተዳደር፤ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈጸም አቅም ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

**ሰ.** የአክስዮን ማኅበሩን የውጪ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ መርምሮ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤

**ሸ.** በአክስዮን ማኅበሩ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል፤ መከላከል ካልተቻለም ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ይሰራል፤

**ቀ.** የአክስዮን ማኅበሩን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሠራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

**በ.** የአክስዮን ማኅበሩን ዋና ስራ አስፈጻሚ ይሾማል፣ይሽራል፤ የስራውንም ዋጋ ይወስናል፤

**ተ**. ለቦርድ ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ይሽራል፤

**ቸ.** ለዋና ስራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን ዋና ስራ አስፈጻሚው ሲያቀርብለት ይሾማል ፤

**ነ.** ቅርንጫፎችን ለማቋቋም የሚቀርብለትን እቅዶች መርምሮ ያፀድቃል፤

**ኘ.** መጠኑ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰን ሆኖ፣ ከፍተኛ መዋዕለነዋይ የሚጠይቁ የቴክኖሎጂ፣ የማይንቀሳቀሱንብረቶችን ወይም የሌሎች ኩባንያዎችን አክስዮኖች መግዛት እና መሸጥ በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፤

የብድር ስምምነቶችን ይፈቅዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ የማኅበሩን ንብረት በመያዣ የማስያዝ ውሳኔዎችን ያፀድቃል፤

**አ.** አክስዮን ማኅበሩን ይወክላል።

**ከ.** ሌሎች በህግ የተሰጧቸውን ስልጣን እና ተግባራት ያከናውናል።

23.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ በሆነ መጠን ሥልጣኑን በውክልና ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የቦርድ አባላት ወይም ለዋናው ስራ አስፈጻሚ ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ ሀያ አራት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

24.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በማኅበሩ ዋና መስሪያቤት ወይም በሌላ ቦታ ሊደረግ ይችላል።

24.2. በማናቸውም ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ዳይሬክተሮች ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይኖራል።

24.3. እያንዳንዱ የቦርድ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል።

24.4. ውሳኔዎች የሚሰጡት በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

24.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሰብሳቢው፣ በምክትል ሰብሳቢው ፣ በሁለት /2/ የቦርድ አባሎች ወይም በዋናው ሥራ አስፈጻሚ ጠያቂነት ይሰበሰባል።

24.6. በማናቸውም የቦርድ ስብሰባ ላይ የተደረገ ውይይት በቃለ ጉባኤ መልክ ተጽፎ በስብሰባው ላይ በተገኙ የቦርድ አባሎች ይፈረማል።

24.7. የቦርድ ስብሰባዎች የሚጠሩት የስብሰባውን አጀንዳ በማያያዝ ከስብሰባው ከሦስት (3) ቀን በፊት ለዳይሬክተሮች በሚደርስ ፅfhፍ ወይም በማንኛውም የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ይሆናል።

24.8. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

24.9. ከስብሰባ የቀረ አንድ ዳይሬክተር የሚወከለው ስብሰባው ላይ በሚገኝ ሌላ ዳይሬክተር ይሆናል፤ የውክልና ሥልጣኑ በፅfhፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ይሰጣል፤ አንድ ዳይሬክተር ሊወከል የሚችለው በአንድ ዳይሬክተር ብቻ ነው።

24.10. የዳይሬክተሮች ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን በቪዲዮ ወይም በሌላ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊያደርግ ይችላል። በቪዲዮ መገናኛ ዘዴ የሚካሄደው ስብሰባ የተሰብሳቢዎቹን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ

የተሳታፊዎችን ድምፅ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት።

24.11. የዳይሬክተሮች ቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባዔ ተፅፈው በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በማኅበሩ ፀሐፊ ይፈረማሉ፤ ቃለ ጉባዔውም ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ ውስጥ ይቀመጣል።

24.12. የዳይሬክተሮች ቦርዱ የራሱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይኖረዋል።

## አንቀጽ ሀያ አምስት

## የአክስዮን ማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

25.1. የአክስዮን ማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል።

25.2. የአክስዮን ማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አግባብ ባላቸው ህጎች፤ በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ጠቅላላ መመሪያ መሠረት የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል። የማኅበሩን የንግድ እንቅስቃሴ ለማሳካት፣ለመቆጣጠርና ለመምራት አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት ሁሉ ይፈፅማል።

25.3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋናው ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

**ሀ.** ለዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያግዙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ በሚፈልጉበት ጊዜ ያቀርባል፤

**ለ.** የማኅበሩን ዓመታዊ ሪፖርት፣ በጀት እና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፣ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

**ሐ.** ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን መርጦ እንዲሾሙ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፤

**መ.** በማናቸውም የአክስዮን ማኅበሩ ሥራ አካሄድ ተግባር እና በፍርድ ቤት በሚታይ ማናቸውም ጉዳይ አክስዮን ማኅበሩን ይወክላል፤

**ሠ.** ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ እና የደመወዝ ስኬል መሰረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ከሥራ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፤

**ረ.** ክፍያዎችን ይፈጽማል፣ ይቀበላል፤ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል ወይንም ይዘጋል፤ በአክስዮን ማህበሩ ስም ንብረት ይከራያል ወይም ያከራያል፤

**ሰ.** የአክስዮን ማኅበሩን ፀሐፊ ቅጥርና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤

**ሸ.** ቦርዱ በሚያወጣው ፖሊሲ መሰረት ፕሮሲጀር፣ ዝርዝር የስራ መመሪያ ወይም ሰርኩላሮችን ያወጣል፤**ቀ.** የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያፀድቀው እቅድ መሰረት ቅርንጫፎችን ይከፍታል፣

**በ.** በአንቀፅ 23 (1)(ኘ) ከተመለከተው ውጪ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ወይም የሌሎች ኩባንያዎችን አክስዮኖች ይገዛል፤ ይሸጣል፤ የብድር ስምምነቶችን ይፈቅዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ የማኅበሩን ንብረት በመያዣ የማስያዝ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

**ተ.** በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሰረት የሚከናወኑ ከፍተኛ መዋዕለነዋይ የሚጠይቁ የቴክኖሎጂ፤ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እና አክስዮኖችን የተመለከቱ የግዢ እና የሽያጭ ውሎችን ይፈራረማል፤

**ቸ.** ከመድን ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳት የደረሰባቸው እና ካሳ የተከፈለባቸውን ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች

የአክስዮን ማህበሩ ንብረቶች እንዲሸጡ እና ስመ ሀብቱ ለሦስተኛ ወገኖች እንዲዛወሩ፤ እንደአስፈላጊነቱ እንዲወገዱ ይወስናል፤

**ኘ.** በአክስዮን ማህበሩ ስም ንብረቶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፤ ይከራያል፣ ያከራያል፤ እንዲሁም የዕዳ ማወራረጃ ሰነዶችን ይፈርማል፤

**አ.** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣኑን ለአክስዮን ማኅበሩ ሠራተኞች፣ ወኪሎች፣ ለኢንሹራንስ ወኪሎች፣ ለሕግ ባለሙያዎች ወይንም ለጠበቆች ውክልና ይሰጣል፣ ይሽራል፤

**ከ.** ከዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ ሀያ ስድስት

## የኦዲተሮች የአገልግሎት ዘመን

የአክስዮን ማኅበሩ ኦዲተሮች የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል። የአክስዮን ማኅበሩ ኦዲተሮች በጠቅላላ ጉባኤ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

## አንቀጽ ሃያ ሰባት

## የኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባር

ኦዲተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፤

27.1. በንግድ ሕጉ መሠረት ለአክስዮን ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን የሂሳብ አሰራሮች መርምሮ የኦዲት ሪፖርትያቀርባሉ፤

27.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የማኅበሩን ትክክለኛ ገፅታ የሚያመለክት መሆኑን ያረጋግጣሉ፤

27.3. የአክስዮን ማኅበሩን መዛግብትና የዋስትና ሰነዶች /ሰክዩሪቲስ/ ይመረምራሉ፤

27.4. የአክስዮን ማኅበሩን የንብረት ዝርዝር መዝገብ፣ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፤

27.5. በሥራቸው ሂደት ውስጥ ያጋጠሟቸውን ትክክለኛ ያልሆኑ አሠራሮች እነደአስፈላጊነቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ፤ ለጠቅላላው ጉባኤ እና ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያሳውቃሉ፤

27.6. በህግ እና በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ።

## አንቀጽ ሀያ ስምነት

## የአክስዮን ማኅበሩ ፀሀፊ

የአክስዮን ማኅበሩ ፀሐፊ ተጠሪነት ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲሆን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

28.1. የአክስዮን ማኅበሩን ጠቅላላ ጉባዔዎች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ኮሚቴዎች ፀሐፊ በመሆን ቃለ-ጉባዔዎችን መያዝ፤

28.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ከመደረጉ ቢያንስ ሦስት ቀናት በፊት የስብሰባውን አጀንዳ እና ሌሎች አግባብነትያላቸውን ሰነዶች ለቦርድ አባላት እንዲደርሱ ማድረግ፤

28.3. ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቶችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፤

28.4. ለባለአክስዮኖች እና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ መስጠት፤

28.5. የባለአክስዮኖችን ጠቅላላ ጉባዔ ማዘጋጀት፣ ቃለ-ጉባዔ መያዝ፣ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ቃለ ጉባዔዎችን በማቅረብ መፅደቁን ማረጋገጥ፣ ቃለ ጉባዔዎችን በጥንቃቄ ማደራጀት እና ማስቀመጥ፣

28.6. በአክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

## አንቀጽ ሀያ ዘጠኝ

## የአክስዮን ማኅበሩ ሂሳቦች

29.1. የአክስዮን ማኅበሩ መዛግብትንና ሂሳቦችን በሕግና በንግድ ሥራ ተቀባይነትን ባገኙ ደንቦችና የአሠራር ልምዶችመሠረት ይያዛል።

29.2. ዋናው ሥራ አስፈጻሚው በዋናው መሥሪያ ቤትና በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ተገቢነት ያላቸው መዛግብትናሂሳቦች መያዛቸውን ያረጋግጣል።

## አንቀጽ ሰላሳ

## የመጠባበቂያ ሂሳብ

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 432 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ከማኅበሩ ትርፍ ላይ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 433(2) መሠረት መጠባበቂያ ሂሳብ መያዝ እንዲቻል ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ማስወሰን ይችላል፤ እንዲሁም ትርፍ ሳይከፋፈል ወደሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ ለጠቅላላ ጉባዔ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል።

## አንቀጽ ሰላሳ አንድ

## የማኅበሩ መፍረስ

31.1. የአክስዮን ማኅበሩ በንግድ ህጉ በተጠቀሱ ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል።

31.2. ከእዳ ክፍያ የሚተርፈው የተጣራ ሂሳብ በተከፈሉ አክሲዮኖች መጠን ለአባሎች ይከፋፈላል።

## አንቀጽ ሰላሳ ሁለት

## የሂሣብ ዓመት

የአክስዮን ማኅበሩ የሂሣብ ዓመት እንደ ኤውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ ጁላይ 1 ቀን እስከ ጁን 30 ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

## አንቀጽ ሰላሳ ሶስት

## የአክስዮን ማኅበሩ ሪፖርቶች

የዳይሬክተሮች ቦርድ ለእያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ እንዲሁም የሥራ ክንውን

ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አራት

## የአክስዮን ማኅበሩ ሕትመት

34.1. አክስዮን ማኅበሩ የሂሣብ መግለጫዎቹን አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡

34.2. አክስዮን ማኅበሩ የራሱ የሆነ ድረ-ገፅ ይኖረዋል፤ ድረ-ገፁን በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 493 እና 494 የተመለከቱት ዝርዝር ሁኔታዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አምስት

## አክስዮን ማኅበሩ የሚቆይበት ጊዜ

አክስዮን ማኅበሩ የሚቆየው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስድስት

## የአክስዮን ማኅበሩን መመሥረቻ ፅfhፍ ስለማሻሻል

ይህ መመሥረቻ ፅfhፍ በንግድ ሕጉ እና የባለአክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሚያስተላልፈው ውሳኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሰባት

## የአክስዮን ማኅበሩ የተሻሻለ የመመሥረቻ ፅfhፍ ማፅደቅ እና መፈረም

ይህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ፅfhፍ ጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም በተደረገው የአዋሽ የኢንሹራንስ አክስዮን ማኅበር ባለአክስዮኖች 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ አፅድቀውታል፡፡ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ቀርቦ ከተፈረመ እና ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡